

# የኢየሱስ እናት ማርያም

- ማርያም በናዝሬት ከተማ ትኖር የነበረች ልጃገረድ ነች። ዮሴፍ ከሚባል ሰው ጋር ለመጋባት ተጫጭተው ነበር። እርሷ አልተገነዘበችውም እንጂ እግዚአብሔር በምድር ከሚኖሩ ሴቶች ሁሉ ይልቅ ለአንድ እጅግ ለከበረና ለተለየ አላማ መፈፀም መርጧት ነበር።

- እግዚአብሔርም ይህንን መልእክት የሚያደርስ መልአክ ላከላት። መልአኩ ገብርኤልም፣ “ሰላም ለአንቺ ይሁን እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው። በእግዚአብሔር ፊትም ሞገስ አግኝተሻል አላት፣” አላት። ማርያም ፈራች። መልአኩ ግን ወንድ ልጅ እንደምትወልድና ስሙንም ኢየሱስ ብላ እንደምትጠራው ነገራት።

- ማርያም የምትወልደው ልጅ ሌላ ማንኛውም ሕፃን በሚወለድበት መንገድ አልነበረም የሚወለደው። ማርያም ምድራዊ እናቱ ነች። አባቱ ግን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እርሱም አማኑኤል ማለትም “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው” ተብሎ ይጠራል። እርሱም እራሱ በሚመሰርተውና መጨረሻ በሌለው መንግስት ንጉስ ይሆናል።

- ማርያምም፣ “እኔ ከቶ ወንድ አላውቅምና ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?” ስትል መልአኩን ጠየቀችው። መልአኩም መልሶ፣ “መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይፀልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፣” አላት።

- ማርያምም መልሳ፣ “እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣” አለችው። ከዚያም መልአኩ ተለይቷት ሄደ።

- መቼም ማርያም ማርገዟን ሲያውቅ የዮሴፍ ድንጋጤ ምን ሊመስል እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ? ገና ጋብቻ አልፈፀሙም፣ እንደ ባልና ሚስት አብረው መኖርም አልጀመሩም። ይህ ሊያዋርዳት የሚችል ነገር ነው። ስለዚህ ጉዳይ ምን ማድረግ እንደሚገባው እያሰበ እያለም መልአክ በሕልም ተገልጦለት፣ “አይዞህ አትፍራ። ማርያምን እንደሚስትህ ልትወስዳት ትችላለህ። አሁን እርሷ የፀነሰችው ከመንፈስ ቅዱስ ነው፣” አለው። ሕፃን እንደምትወልድና ስሙን ኢየሱስ ብላ እንደምትጠራውም ነገረው።

- ስለዚህም ዮሴፍና ማርያም በእቅዳቸው መሠረት ተጋቡ። ሰዎች ከማግባቷ በፊት እንዳረገዘች ጠርጥረዋት ይሆን? ዮሴፍና ማርያም እውነቱን ያውቁታል። እርሷ በማህፀኗ የተሸከመችው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያውቃሉ።

- ሌላ ይህን ምስጢር የምታውቀው የማርያም ዘመድና የመጥምቁ ዮሐንስ እናት የሆነችው ኤልሳቤጥ ናት። ማርያም በአንድ ወቅት እርሷን ጎብኝታታለች። በዚያን ጉብኝት ጊዜም ማርያም መልአኩ ገብርኤል ተገልጦላት ያላትን ሁሉና ከዚያ በኋላ በሕይወቷ የሆነውን ሁሉ አጫውታታለች።

- ኢየሱስ የሚወለድበት ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣም ማርያምና ዮሴፍ ወደቤተልሔም ከተማ ግብር ለመክፍል መሄድ ነበረባቸው። ቤተልሔም እንደደረሱም የእንግዳ ማረፊያዎች በሙሉ ለተመሳሳይ ጉዳይ ከተለያዩ ቦታዎች በመጡ እንግዶች ተሞልተው ነበርና ማረፊያ ማግኘት አልቻሉም። ለእነርሱ የተገኘላቸው ማረፊያ ቦታ የከብቶች ማደሪያ ብቻ ነበር። የወለደችውንም ልጇን ወደቤተልሔም ስትጓዝ ይዛ ባመጣችው ጨርቅ ጠቀለለችው።

- የኢየሱስን መወለድ የምስራች በመጀመሪያ የሰሙት በጎቻቸውን ሲጠብቁ የነበሩ እረኞች ናቸው። መልአክ ተገለጠላቸውና፣ “አትፍሩ፣ ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን የምስራች ይዤላችሁ መጥቼአለሁ። ዛሬ በዳዊት ከተማ መድሃኒት እርሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ ተወልዶአል፣” አላቸው። ወዲያውም በሰማይ ላይ ብዙ መላእክት ታዩ። እረኞቹም በፍጥነት ኢየሱስ ወደተወለደበት ቦታ ሄዱ። ከዚያም ለሰዎች ሁሉ ያዩትንና የሰሙትን መመስከር ጀመሩ።

- ማርያምና ዮሴፍም በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ልጁን በፍቅርና በጥንቃቄ ማሳደግና መንከባከብ ጀመሩ። አንድ ጊዜ መልአክ በሕፃኑ ላይ አደጋ እንደሚደርስበት ሲነግራቸው ወደ ግብፅ ይዘውት ሸሹ።

- ኢየሱስ አርባ ቀን በሞላው ጊዜ ወደቤተ መቅደስ በወላጆቹ ተወሰደ። በዚያም ስምኦን የሚባል ነቢይ ማርያምን እንዲህ አላት፣ “እነሆ፥ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ፥ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፥ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል፣” አላት።

- እውነትም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰላሳ ሶስት ዓመታት በኋላ ሲሰቀል ስትመለከት የማርያም ነፍስ ተወጋ።

*ስለማርያም ታሪክ በሉቃስ ወንጌል ምእራፍ 1 እና ምዕራፍ 2 ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ።*